የማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 11 እና 12

1. "ጌታ ጌታዬን 'ጠላቶችህን ከእግርህ ጫማ በታች እስካደርጋቸው ድረስ በቀኝ ተቀመጥ' አለው" ይህ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ በየት ይገኛል?
ሀ)በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 12
ለ)በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 22
ሐ)በመዝሙር 109(110)
መ)ሁሉም

2. “ ምን ታደርጋላችሁ ያላችሁ ሰው ቢኖር ጌታ ይሻዋል በሉ” በተባሉት መሰረት ይህንን ሲመልሱ ባለቤቶቹ እንዲወስዱ እንዴት ፈቀዱላቸው?
ሀ) አህያይቱን አይፈልጓትም ነበርና
ለ) አስፈራርተዋቸው
ሐ) አህያይቱ የተሰረቀች የሰው ገንዘብ ነበረችና
መ) መልስ የለም

3. በማርቆስ ወንጌል የሆሣዕና ታሪክ እና በማቴዎስ ወንጌል የሆሣዕና ታሪክ መካከል ምን ልዩነት አለ?
ሀ)በማቴዎስ ወንጌል ላይ ሕዝቡ ልብሳቸውን

አያነጥፉም
ለ) በማቴዎስ ወንጌል ላይ አህያ እና ውርንጫ አምጡልኝ ሲል በማርቆስ ወንጌል ውርንጫ ብቻ ነው ያለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
ሐ)በማርቆስ ወንጌል ላይ አህያ እና ውርንጫ አምጡልኝ ሲል በማቴዎስ ወንጌል ውርንጫ ብቻ ነው ያለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
መ)ሁሉም

4. ጌታችን የተመለከትት ፍሬ የሌላት ቅጠል ብቻ ያላት ዛፍ በምን ትመሰላለች?
ሀ) ጌታዋ በደንብ ያልተንከባከባት እርሻ
ለ) ጠባቂ መልአክ በራቃት ነፍስ
ሐ) በጎ ምግባር ትሩፋት የሌላት ነፍስ
መ) ለ እና ሐ

5. ፍሬ በማጣት የተረገመችው ዛፍ የምን ዛፍ ናት?
ሀ)የበለስ ለ)የዘይቱን ሐ)የወይራ
መ)የሾላ

6. በበዓለ ሆሣዕና የምናስረው ዘንባባ አመጣጡ

ከምንድን ነው?
ሀ)ሕዝቡ የዘንባባ ዝንጣፊ ማንጠፋቸውን
ለ) ጌታችን በአህያ ላይ መቀመጡ
ሐ)ሁለቱ ሐዋርያት አህያይቱን መፍታታቸውን
መ)ምንም አያገናኘውም

7. ሆሣዕና ማለት ምን ማለት ነው?
ሀ) ልደት ለ) መድኀኒት ሐ) ደስታ
መ) ጤና

8. በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ብሩክ ነው ብሎ የተናገረው የመጀመሪያው ሰው ማን ነው?
ሀ) ያዕቆብ
ለ)ከሐዋርያት አንዱ
ሐ)የኢየሩሳሌም ሕዝብ
መ)መዝሙረኛው ዳዊት

9. በቅዱስ ማርቆስ ወንጌል ላይ በተቀመጠው መሰረት ጌታ የረገማትን ዛፍ መቼ ደርቃ አገኟት?
ሀ) ጌታ በረገማት በማግስቱ
ለ) ሰኞ

ሐ) ማግሰኞ
መ) ሀ እና ሐ
ሠ) ሀ እና ለ

10. ጌታ ሐዋርያት ሰው ያልተቀመጠባትን የአህያ ግልገል እንዲያመጡለት የላካቸው ወዴት ነው?
ሀ) ቤተ ፋጌ
ለ) ቤተልሔም
ሐ) ቢታንያ
መ) ሀ እና ሐ

11. ጌታ በምኩራብ ሳለ ጸፎችና ሊቃነ ካሕናት “በማን ስልጣን ይህንን ታደርጋለህ” ባሉት ጊዜ ምን አደረገ?
ሀ) ዝም አላቸው
ለ) ገርፎ አስወጣቸው
ሐ) ጥያቄን በጥያቄ መለሰላቸው
መ) በማን ስልጣን እንደሚያደርግ ነገራቸው

12. በሆሳዕና ማግሥት ከተፈጸሙት ውስጥ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) መርገመ በለስ

ለ) አንጽሆተ ቤተመቅደስ
ሐ) ቁርባን
መ) መልሱ የለም

13. ሊቃነ ካህናት እና ጸሐፍት ጌታን ለመያዝ የፈሩት ለምን ነበር?
ሀ) በመምህርነቱ አክብረውት
ለ) በአምላክነቱ ይገስጸናል ብለው
ሐ) ሕዝቡ ሁሉ ትምህርቱን ያደንቁ ነበርና
መ) ሀ እና ሐ

14. በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 12 ላይ የወይኑ ባለቤት ለሦስተኛ ጊዜ ልኮት የገደሉት አገልጋይ የማን ምሳሌ ነው?
ሀ) የካህኑ ዘካርያስ
ለ) የመጥምቁ ዮሐንስ
ሐ) የሐዋርያት
መ) የጌታችን

15. ሰዱቃውያን ማለት እነማን ናቸው?
ሀ) የአይሁድን ታሪክ ጽፈው የሚያስቀምጡ

ለ) ትንሳኤ ሙታን የለም የሚሉ
ሐ) የአይሁድ ካህናት
መ) የአይሁድ መምህራን

16. ከትእዛዛት ሁሉ የምትበልጠው ...
ሀ) ጾም
ለ) ጸሎት
ሐ) እግዚአብሔርን በልብ ሁሉ መውደድ
መ) ባልንጀራን እንደራስ መውደድ

17. ሁለት መሐለቅ በሙዳየ ምጽዋት ያገባችው ሴት ...
ሀ) ከሌላት ላይ ስለሰጠች ከሁሉ አብዝታ እንደሰጠች ተቆጠረላት
ለ) በኃጥአን ነፍስ ትመሰላለች
ሐ) የጌታ የቅርብ ዘመዱ ነበረች
መ) ሀ እና ለ

18. ከሚከተሉት ውስጥ ከሰዱቃውያን ወገን በመሆን የሚታወቀው የቱ ነው?
ሀ) ቶማስ ለ) ዮሐንስ ሐ) ገማልያል መ) ጳውሎስ

19. በወይኑ ባለቤት ምሳሌ ላይ ባለቤቱ የላካቸው አገልጋዮች እና ልጁ የማን ምሳሌ ናቸው?
ሀ) አገልጋዮች የመላእክት፣ ልጁ የጌታ
ለ) አገልጋዮች የነቢያት፣ ልጁ የጌታ
ሐ) አገልጋዮች የምእመናን፣ ልጁ የካህናት
መ) ሀ እና ለ

20. ከሚከተሉት ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለረገማት በለስ ምሳሌ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) በጎ ሚሰራ ሰው ያልተገኘባትን የኢየሩሳሌም ከተማ መልካም ሰው አይውጣብሽ እንዳላት
ለ) በአንጻረ በለስ ባንቺ ፍዳ በመጣ የሚያዝ አይኑር ብሎ ኃጢአትን እንደረገመ
ሐ) ሃይማኖት እና ምግባር ያለው ሰውን እግዚአብሔር እንደሚረግመው
መ) ሁሉም